**ትርጉም የሚፈልግ መረጃ፦**

የዴልታ ዝርያ የ COVID-19 ህመም በማንኛውም ሰዓት በሚያስገርም ሁኔታ ሊጨምር እንደሚችል አረጋግጧል። ለሰራተኞችዎ ከመተንፈሻ ጉዳቶች፣ ለምሳሌ COVID-19 ን ከሚያስከትለው ቫይረስ፣ የሚጠብቅ የመተንፈሻ መከላከያ (N95) ማቅረብ በ Washington Department of Labor and Industries (L&I፣ በዋሺንግተን የስራ እና ኢንዱስትሪዎች መምሪያ) ቁጥጥር የሚደረግበት እና ተግባራዊ የሚሆን የደህንነት ደንብ ነው። የፊት ምርመራ የ N95 መተንፈሻ በትክክል ጥቅም ላይ ሲውል በትንፋሽ የሚተላለፈውን ቫይረስ 95% እንደሚያጣራ ያረጋግጣል። የፊት ምርመራ እንዲያደርጉ እና መተንፈሻውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ በማዘጋጀት ሰራተኞችዎ እንዲሰሩ ያድርጉ።

የ DOSH Directive 11.80 Temporary Enforcement Guidance (አቅጣጫ 11.80 ጊዜያዊ የአፈጻጸም መመሪያ) (https://lni.wa.gov/dA/1d2a778d31/DD1180.pdf) (በእንግሊዘኛ ብቻ) በሴፕቴምበር 21፣ 2021 ዘምኗል። L&I አመታዊ የፊት ምርመራ መስፈርትን ተፈጻሚ ማድረግ በጃንዋሪ 1፣ 2022 ይጀምራል። ይህም ማለት፣ ለምሳሌ፣ ሰራተኞችዎ በ 11/1/2020 የፊት ምርመራ አድርገው ከነበረ፣ በ 11/1/2021 እንደገና የፊት ምርመራ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ምርመራ ካላደረጉ፣ አመታዊ የፊት ምርመራ ባለማድረግ በጃንዋሪ 1፣ 2022 ተቋምዎ ሊጠቀስ ይችላል።

Department Of Health (DOH፣ የጤና መምሪያ) በለይቶ ማቆያ ወይም በኳራንቲን ውስጥ ላሉ ነዋሪዎች/ደንበኞች እንክብካቤ ለሚሰጡ ክብካቤ ሰጪዎች የሚያቀርበውን አገልግሎቶች የመጠቀሚያ ሰዓቱ አሁን ነው – ነጻ የህክምና ምርመራ እና ለመተንፈሻ አጠቃቀም የፊት ምርመራ። ይህ አቅርቦት በ 2021 መጨረሻ ይጠናቀቃል።

ስለ Respiratory Protection Program ለበለጠ መረጃ የ DOH Respiratory Protection Program (የመተንፈሻ መከላከያ ፕሮግራም) ድረገጽን (https://www.doh.wa.gov/ForPublicHealthandHealthcareProviders/HealthcareProfessionsandFacilities/HealthcareAssociatedInfections/RespiratoryProtectionProgram) (በእንግሊዘኛ ብቻ) ይጎብኙ። Washington State Department of Health፣ ወይም በ HAI-FitTest@doh.wa.gov ኢሜይል ያድርጉ።